# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251 116– 55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia e-mail:-allethiopiaunityparty@gmail.com

# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY


ቁጥር
Ref No. ____________
ቀን
Date____________

## ገዥው ፓርቲ በመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች ላይ እያደረሰ ያለው ሰቆቃ ቀጥሏል።

መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በሃገራችን ረሃብ፣ በሽታ፣ ማይምነትና ድህነት እንዲወገዱ፣ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣትና ሌሎችም መብቶች እንዲከበሩ፣ ሰዎች በእኩልነት እንዲዳኙ፣ ዜጎች በመረጧቸው መሪዎች እንዲተዳደሩ ባጠቃላይ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ የሚታገል ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑ ይታወቃል።

ፓርቲው በሃያ ዓመቱ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴው እጅግ ከባድ የተሰኙ መስዋዕትነቶችን ከፍሏል። መሪውን ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን ሰማዕት እስከማደረግ ድረስም ዋጋ ከፍሏል። ከከተማ እስከ ገጠር ባሉ አባሎቻችን፣ ደጋፊዎቻችንና ጽ/ቤቶቻችን ላይ የገዥው ፓርቲ በርካታ በደሎችን ሲፈጸምብን ቆይቷል። አሁንም እየፈጸመብን ይገኛል።

### ከእነዚህ ውስጥም በአማራ ክልል÷

1. አቶ እንዳልክ አታሌ በሰሜን ጎንደር ዞን የምስራቅ በለሳ ወረዳ የመኢአድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የገዥው ፓርቲ ታጣቂዎች አፍነው ከግንቦት 28/2003 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 03/2003 ዓ.ም. ድረስ ለአምስት ቀናት ሰውረዋቸው ቆይተዋል። ከዚያም ወደ አምባ ጊዮርጊስ በመውሰድ ችሎት አቅርበው የሃሰት ክስ መስርተው የሃሰት ምስክር በማቅረብ ስምንት (8) ዓመት እስራት እና የብር አንድ ሺ (1,000.00) ቅጣት ተወስኖባቸው በአሁን ወቅት በዳባት እስር ቤት ይገኛሉ።

2. በምስራቅ ጐጃም ዞን ሁለት እጁ እነሴ ወረዳ የመኢአድ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊን አቶ ገብሬ ዘመረን፣ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊን ወ/ሮ ፀሀይ ዘለቀን እና የወጣቶች ጉዳይ ተወካይን ወጣት ብርሃኑ ዘለቀን የወረዳው ፖሊስ አዛዥ የሆኑት ኢንስፔክተር አደራጀው፣ ም/ኢንስፔክተር አማረ እንዲሁም የወረዳ ሚሊሺያ ተጠሪ የሆኑት አቶ ጥላሁን ሙናቻ፣ አቶ ብሬ ጀምበሩ እና የቀበሌ ታጣቂዎች መስከረም 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከደብረ ጉባዔ ቀበሌ ይዘው አባያ በረሀ በመውሰድ ደብድበዋቸዋል። ከመኢአድ መውጣት አለባችሁ እያሉም አንገላተዋቸዋል። መኢአድ ውስጥ ሆኖ የትጥቅ ትግል ከሚያደርጉት ጋር ግንኙነት ያለውን ንገሩን እያሉ ሲያሰቃዩአቸው ከቆዩ በኋላ አስረዋቸዋል። እነሱ በታሰሩ በሁለተኛው ቀን ከላይ የተገለፁት የገዥው ፓርቲ አካላት ቤታቸውን ሰብረው በመግባት ከከተማ ይዘው የሄዱትን ፎርጅድ ብር እና ልዩ ልዩ ጨርቆች ከእነሱ ቤት እንደተገኙ አድርገው በሀሰት በመወንጀል ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ክስ መሰርተውባቸው
   - 1ኛ/ አቶ ገብሬ ዘመረን የተዘረፏቸው 5,000.00 ብር እና ንብረት ሳያንስ 4 ዓመት እስራትና የብር 1,000.00 (አንድ ሺ ብር) መቀጫ፣
   - 2ኛ/ ወጣት ብርሃኑ ዘለቀን 3 ዓመት እስራትና የብር 800.00 (ስምንት መቶ ብር) መቀጫ እና
   - 3ኛ/ ወ/ሮ ፀሀይ ዘለቀን የ6 ወር ህፃን ልጅ ይዘው በግፍ 2 ዓመት እስራት እና 500.00 ብር መቀጫ ተወስኖባቸዋል።

3. አቶ ጌታሁን አመኑ የመተከል ዞን የመኢአድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና የመኢአድ ማዕከላዊ ምክር ቤት አባል ሲሆኑ ‹‹ከ2 ዓመት በፊት ሰው ተደባድበሃል›› በሚል የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው የአንድ (1) ዓመት

እስራት ተፈርዶባቸው ከመጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ላይ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ በሌላ የሃሰት ክስ ብር አምስት ሺ (5,000.00) እንዲቀጡ ተደርገዋል።

4. አቶ መስፍን በላቸው የተባሉ የመኢአድ አባልን የገደሉት አቶ ደስታው በላቸው በአሁን ሰዓት ከእስር ተፈትተው እና መሳሪያ ተሰጥቷቸው የመኢአድ አባላትን በማስቃየት ላይ ይገኛሉ።

5. ከዚህ በፊትም በምርጫ 97 የምሥራቅ በለሳ ወረዳ ክልል ምክር ቤት መኢአድ ቅንጅትን ወክለው የተወዳደሩ አቶ ምሳ ዮሃንስ በታጣቂዎች መገደላቸው ይታወሳል።

6. አቶ ብርሃኑ አቡሃይ የሰሜን ጎንደር ዞን የምስራቅ በለሳ ወረዳ መኢአድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢን ነሃሴ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሠዓት ላይ ከቤታቸው በር ላይ የገኘው ፓርቲ ታጣቂዎች የሆኑት አቶ አለልኝ ወንድአሁን ቸኮል እና አቶ ቁምለት አሰፋው ቸኮል ግንባራቸውን፣ ጀርባቸውንና ክንዳቸውን በመጥረቢያ ጨፍጭፈዋቸዋል።

## በደቡብ ኢትዮጵያ፦

1. በደራሼና ኮንሶ አካባቢ ሰገን ዞን ከማሳቸው እንዲለቁ የተጠየቁ ሰማንያ ሦስት (83) የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች መሬታችንን አንለቅም በማለታቸው ነሃሴ 3/2003 ዓ.ም ጀምሮ እንዲታሰሩ ተደርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሰባ (70) ያህሉ እስረኞች ከ10 እስከ 15 ቀናት ያህል ከታሰሩ በኋላ ሲፈቱ ቀሪዎቹ አስራ ሦስት (13) ሰዎች ግን አሁንም ድረስ እንደታሰሩ ናቸው። አሁንም በእስር ከሚገኙት ውስጥ አቶ ኩካዮ ደዲኮ የደራሼ ዙሪያ ወረዳ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይገኙበታል። ከሰማንያ ሦስቱ ሰዎች መካከል 80 በመቶ ያህሉ የመኢአድ አባላት ሲሆኑ 20 በመቶ ያህሉ የመኢአድ ደጋፊዎች ናቸው።

2. አቶ ታምሩ ቲቶ የደራሼ ዙሪያ ወረዳ የመኢአድ ጽ/ቤት ገንዘብ ያዥ ሲሆኑ የሃሰት ክስ ተመስርቶባቸው ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ ‹‹ችሎት ደፍረሃል›› በሚል ከሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የ 4 ወር እስራት ተፈርዶባቸዋል።

3. በጎፋ ልዩ ዞን በኡባ ደብረ ፀሃይ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ አራት (4) የመኢአድ አመራር አባላት ማለትም፦

1ኛ/ አቶ እያሱ ኦዳላ - በኡባ ደብረ ፀሃይ ወረዳ የሻላ ቀበሌ የመኢአድ ሰብሳቢ

2ኛ/ አቶ ዓይናለም ብርሃኑ - በኡባ ደብረ ፀሃይ ወረዳ የቆርባ ቀበሌ የመኢአድ ሰብሳቢ

3ኛ/ አቶ ጉደታ ጉታ - በኡባ ደብረ ፀሃይ ወረዳ የቡነ ወይሴ ቀበሌ የመኢአድ ሰብሳቢ

4ኛ/ አቶ ወራሶ ወጌታ -በኡባ ደብረ ፀሃይ የቆርባ ወረዳ ቀበሌ የመኢአድ ም/ ሰብሳቢ

ከጥቅምት 21/2004 ዓ.ም ጀምሮ በአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደርገው ጥቅምት 29/2004 ዓ.ም. በዋስ ተፈትተዋል። የታሰሩትም ከመኢአድ ጽ/ቤት ከስብሰባ ላይ ተወስደው ነው። ከአራቱ የመኢአድ አመራር አባላት ውስጥ አቶ ወራሶ ወጌታ እራሳቸውን እስከ መሳት የሚያደርስ ከባድ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል።

4. አቶ ገረመው ገለቦ የደራሼ ዞን መኢአድ ሥር አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ወደ ኮንሶ ወረዳ ቤተ ሰብ ለመጠየቅ ሲሄዱ ‹‹ለምን ትመላለሳለህ?ፖለቲካህን ልታራምድ ነው።›› ተብለው ክስ ሳይመሰረትባቸው ከነሃሴ 6 እስከ 20/2003 ዓ.ም. ለአስራ አምስት ቀናት ያህል በግፍ ታስረዋል።

5. መቶ አለቃ አደይ አንጀሎ የወላይታ ዞን የመኢአድ ዋና ጸሃፊ ጥቅምት 16/2004 ዓ.ም. በወላይታ ዞን የሚገኙ የተለያዩ መንግሥታዊ አካላት በዱላ ደብድበው በቁጥጥር ሥር አውለው ከሦስት ቀን እስር በኋላ ፈትተዋቸዋል።

በተጠቀሰው ዕለት መቶ አለቃ አደይ አንጀሎ በግል የሥራ ቦታቸው ላይ እያሉ ቁጥራቸው ሰላሳ የሚደርሱ በሶዶ ከተማ የአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማው የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፣ የክፍለ ከተማው ፖሊስ ጽ/ቤት፣ በአራዳ ክፍለ ከተማ የሰላም ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የተለያዩ ግብረ ኃይሎች ጠመንጃዎችና ዱላዎች በመያዝ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ሄደዋል። መኖሪያ ቤታቸው እንደ ደረሱም ልጆቻቸውን እያስፈራሩና እየደበደቡ በማስር ከሚኖሩበት የቀበሌ ቤት እንዲለቁ አድርገዋቸዋል። መቶ አለቃ አደይ አንጀሎ እየሠሩ ያሉትን ቤት ሳይጨርሱ ከሚኖሩበት ቤት ተገደው በመውጣታቸው ለችግር ተዳርገዋል።

6. የቦሎሶ ቦንቤ ወረዳ መኢአድ ምክትል ሰብሳቢ የሆኑትን አቶ ታደሰ ኡሬን ጥቅምት 15/2004 ዓ.ም. የመኢአድ ቲ-ሸርት ለብሰሃል በማለት የቀበሌ ታጣቂዎች <u>ለሁለት ቀናት</u> ያህል አስረዋቸዋል፡፡

7. የሶዶ የመኢአድ ሰብሳቢ አቶ መተኪያ መናን ጥቅምት 12/2004 ዓ.ም. በሶዶ ከተማ በመሃል ክፍለ ከተማ በጎላ ቀበሌ የሚገኘውን በስማቸው ግብር ሲከፍሉ የቆዩበትን የምርት ይዞታ ካርታ የለህም እያሉ ደብድበዋቸዋል፡፡ የታጠረውን አጥር በማፈራረስም በይዞታቸው ላይ የሚገኙትን ግምታቸው ሃምሳ ሺ (ሃምሳ ሺ) የሚደርስ ሰብሎች፣ አትክልቶች፣ የተለያዩ የፍራፍሬ ዛፎች በማውደም ከጥቅም ውጭ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ የተፈጸመባቸውን በደልም አቤት ቢሉም ሰሚ አላገኙም፡፡

8. በወላይታ ዞን የመኢአድ አባላት እየተንቀሳቀሱ ባሉባቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች የመኢአድ አባላትን ለማጥቃት የዞኑ የመንግሥት ባለሥልጣናት ግብረ ኃይሎችን በስውር በማሰማራት አንዳንድ የትንኮሳ (የማሸበር) ተግባራት በመፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡ በስውር ትንኮሳቸውም በጎሳና በሃይማኖት ድርጅቶች ግጭቶች እንዲነሱ በሚፈጽሟቸው ሴራዎች ብጥብጥ እንዲነሳ ያደርጋሉ፡፡ በሚነሳው ብጥብጥም የመኢአድ እጅ አለበት በማለት በአባሎቻችን ላይ የማሳደድ ተግባር ይፈጸማሉ፡፡ ለምሳሌም ያህል በሁምቦ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ድርጊቱን በመፈጸም ላይ ናቸው፡፡

<u>በአፋር ክልል</u>÷

አቶ አቡከር አህመድ የተባሉ በአፋር ክልል የሚኖሩ የመኢአድ አባል ‹‹የጎሳህ አባላት መሬታቸውን እንዲለቁ አድርግልን›› ተብለው በገዥው ፓርቲ ሰዎች ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው <u>ከመስከረም 14/2004 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡</u>

እኛ የመኢአድ አባላት ጥንትም ወደ ትግሉ ስንገባ ድል ለማግኘት ዋጋ መክፈል እንዳለብን አምነን በመሆኑ በኢህአዴግ የአፈናና የረገጣ አገዛዝ የማንበገርና ትግላችንንም የማናቋርጥ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እንገልፃለን፡፡ ገዢው ፓርቲ መኢአድን ለማጥፋት በገጠርም ሆነ በከተማ በጠንካራ አመራሮቹና አባላቱ ላይ የሚፈጽመውን ከፍተኛ የሆነ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ለማስቆም የኢትዮጵያ ህዝብ እና ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከጐናችን ትቆሙ ዘንድ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/
ህዳር 5 ቀን 2004 ዓ.ም